# ቴዲ ተለጎመ እንጂ አልተፈታም

ከመላኩ ጸጋዬ መኮንን

## መታሰርስ ታሰር ነገ ትፈታለህ
## ወዳጅ ጠላትህን ትለይበታለህ

ይህ የቆየ አባባል የሚያስረዳው የሰው ልጅ ከህገ አራዊት ስርአት ወጥቶ በሕግ በተደነገገ ስርአት ለመዳኘት በሚያደርገው ትግል በክፉውና በደጉ መካከል በሚደረግ ውጣ ውረድ በግለሰቦች ሕይወት ላይ የሚደርሰውን በውሸት በእስር መንገላታትና ብሎም ከእስር መፈታት በኋላ እውነት ወጥቶ ለመመልከትና ለመታዘብ የሚቻልበትን ራይ የሚጠቁም ነባር አባባል ነው። ወደ ዋናው ጉዳይ ከመግባቴ በፊት እኔም አንድ የግጥም ስንኝ እንድወረውር ይፈቀድልኝ፡

ቁም ነገሩ ቀርቶ ሀገርን ማልማት
ሰቆቃን ማስወገድ ድህነትን ማጥፋት
ከውርደት መላቀቅ ከልመና መውጣት
ሥራችን ከሆነ አንዱ አንዱን መሸንቆጥ
እንደተለመደው እርስ በእርስ መፋጠጥ
የእርስ በእርስ መፋገጥ
አይን ያለው ይመልከት ጆሮ ያለው ይስማ
ሀገር መጥፋቱ ነው እኛ ሳንስማማ
በአንድነት ተነስተን ዛሬ ካልታደግናት
ኢትዮጵያ እናታችን በመኮስመን ላይ ናት

ይህ የሀገር ችግር፡ የሕዝብ ብሶትና ሰላም እጦት፡ የገዥዎች መከፋፈል ሥራ፡ ሰላም የነሳው ቴወድሮስ ካሳሁን /ቴዲ አፍሮ/ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ብርሀን ለመፈንጠቅ ያለውን ምኞት ላምባዲና በሚለው ዜማው የገለጸው ።

ቴዲ አፍሮ ኢትዮጵያ የተሸከመችው አሜካላ ከበደው፡ አስጨነቀው፡ ሰላም ነሳው፡ የወጣትነት እድሜውን ተሻማበት፡ ከእርሱ አልፎ የመጭው ትውልድ እድል አሳሰበው።በመሆኑም በዘመኑ በሀገሪቱ የመገናኛ ብዙሀን፤ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ እርከን ላይ የሚገኙት ባለስልጣናትና ካድሬዎች አማካኝነት በመሰበክ ላይ ያለው የመጠላላት፡ የመበቃቀል፡ የመከፋፈል፡ የመወነጃጀልና ብሎም የቋንቋ ካብ መኮልኮሉን በሚገባ የተረዳው ቴወድሮስ ካሳሁን ይህንን ሰው ሰራሽ የኮሸሺሌ አጥር ረግጦት ወጣ።

በግጥሞቹ ደግነትን፡ ፍቅርን፡ አንድነትን፡ ሰላምን፡ መከባበርን፡ መቻቻልን መደማመጥን፡ እኩልነትን ሰበከ፡ ዘፈነ፡ ዘመረ፡ ታሪክን፡ የሀገር ኩራትን አበሰረ፡ ቂም ያዘለው ልቦና እንዲለዝብ፡ ቀዝቃዛ ውሃ ደፋበት የሚሳለው ጎረዴ እንዲዶሎዱም፡ ከጎጥና ከቋንቋ ልዩነት ባሻገር ትልቋ ሀገር ኢትዮጵያ እንድትታሰብ፡ የተዋረደው፤ የተጣለው፤ የተሰደበው እንዲታሰብ አበክሮ ዘመረ ከሁሉም በላይ የሀገር ስሜትና አርበኝነት እንዲነሳሳ ባንዲራውን በማውለብለብ እንደ አባር በእጁ፡ እንደክታብ ባንገቱ፡

እንደባርኒጣ በጭቅላቱ ደፍቶና እንደሻሽ አስሮ፣ እንደቀበቶ ታጥቆ ክብርና ሞገስ ሰጥቶ፣ ስለአንድነት፣ ስለታሪክ፣ ስለአብሮ መኖር፣ በሚያማምሩ የግጥም ስንኞቹ ገጠመ፣ ገለጸ፣አስረዳ፣ ይሕንኑ በመረዋ ድምጹ አንቆረቆረው፣አዜመ፣ በመልክቱ ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን አምላኩን ጭምር ተማጸነ፤ ለመነ፣ በየግጥም ስንኞቹ በምስል የተቀነባበረ እውነታን በገሀድ አውጥቶ አሳየ።ከብዙ ቃላት የምስል ገላጭነት ባሕሪ ስልትን በመጠቀም የታሪክ እውነታን አንጸባረቀ፤የተደበቀውን አሳዬ፤ እውነታውን በአደባባይ ይፋ አደረገ፤ አንገቱን የደፋውና ቀን የመሸበት ኢትዮጵያዊ እንደገና የሀገሩ ተስፋ እስትንፋስ እንዲዘራበት አደረገ። የወደፊቱን የሀገር ራይ በረጅሙ ትውልዱ እንዲያነጣጥር የሚያስችል መንገድ ለአዲሱ ትውልድ መሪ ጎዳና ጠረገ።በባንዲራው ምሳሌነት የመንደሩን የመከፋፈል ቅስቀሳ አከሸፈው ጠላትን የታሪክ ሀፍረት አከናነበው።

ጀግናን ጊዜና ወቅት ያፈራዋል እንደሚባለው ዛሬ የሀገራችን አንዱ የታሪክ ሰውና ጀግና ቴወድሮስ ካሳሁን ለመሆኑ ማጋነን አይደለም። የጀግና ትርጉም አገባቡ ውሉ ካልጠፋብን በስተቀር የቴዲ ጀግንነት ከማንኛችንም የላቀ ነው። መድፍና ታንክ የታጠቀን ነፍጥ አንጋቢና የማሰብ ኃይሉ በጠመንጃ ገላጋይነት በተሸበበ የህገ አራውት ስርአት ውስጥ እውነትን እና ድምጹን ብቻ ይዞ የሰላሙን ጦር እሜዳ ዋኘበት ሽህ አእላፍ ኢትዮጵያዊያን ከጎኑ አሰልፎ አማለለ፤ አብረው እንዲዘምሩ አደረገ ብሶታቸውን አስተጋባ።የቴዲ መልክት ከሙዚቃ አዳራሽ ውጥቶ ወደ ጎጆ ቤቶች ገባ። ከቡና ተርቲመኞች እስከጣሳ ቤት ደንበኞች፣ ከጠጅ ቤቶች እስከ ቡናቤቶች ከእድር እስክ ሀይማኖት ተቋማት ከህጻን እስከ አዛውንት በሁሉም ጾታና ብሄረሰብ መልክቱ ከምስራቅ፣ ደቡብ፣ ከምእራብ ሰሜን ሳይል ዙሪያውን አስተጋባ በአለም ዙሪያ በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሳይቀር ውቅያኖስና ወንዝ ሳያግደው ከአጥናፍ አጥናፍ አስተጋባ የሁሉንም ጀሮ ዳሰሰው የሞራል ተሀድሶ ሰጠው የኢትዮጵያን ብሩህ ተስፋ ጭላጭል አሳየ።

ያለሕዝብ ፈቃድ የተነጠቀችውን ኤርትራን ጉዳይ ጨመሮ እንደ በርሊን ግንብ ከሁለቱ አባገነን ቡድኖች መውደቅ በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀሏ አይቀሬ እውነት መሆኑን እንዳልከዳሽ ቃል ኪዳን አለብኝ በሚለው ዘፈኑ የተለያዩ ቤተሰቦች እንደሚገናኙ ተነበየ። መቸና እንዴት ሊዋሃዱ ይችላሉ የሚለውን በቀላሉ መልስ መስጠት ቢያዳግትም የኢትዮጵያ ሕዝብና የኤርትራ ሕዝብ ወሰን አሁንም በጠመንጃ ቢታጠርና ቢከለልም ሕዝቡ ሕሊናው ቤተሰብነቱ አልተቆረጠም በምንም መልኩ አገዛዞቹ ይቆረጣሉ እንጂ አንድ ሕዝብ በጠመንጃ አስገዳጅነት ተለያይቶ ሊቀር አይችልም። ጊዜና ወቅት ሲመቸው በአግባቡ ይፈታዋል ይህ አይቀሬ እውነታ ነው። እዚህ ላይ የብዙ ሰዎችን አመለካከት የሚሻሙ ጉዳዮች መኖራቸው ግልጽ ነው ይኸውም ከተባበሩት መንግሥታ የኤርትራ እውቅና ማግኘት ጀምሮ ጦርነቱ የፈጠርው መቃቃርና የገዥዎቹ ወቅታዊ ቅስቀሳ ተደምሮበት ያወናበዳቸው በዚህ መልክ ቢያስቡ ብዙም አያስደንቅም፤ ከዚህም አልፎ እኮ ብዙ ሕይወት በከንቱ አልቋል ከንጉሱ ጀምሮ እስከ ደርግ ዘመን የ17 አመታት ጦርነት፤ ሌላው ይቅርና ያለፈው በሁለቱ ትግርኛ ተናጋሪ አገዛዞች በባድሜ ጦስ የተቀሰቀሰው ጦርነት ከግራ ቀኙ የወደቁት ኢትዮጵያዊያንና ኤርትራዊያን ቁጥር ቀላል አይደለም።

ቴዲ በተፈጥሮ የተሰጠው ድምጽ ብቻ ሳይሆን የግጥም ችሎታውን አካቶ የተዋጣለት የፊልም ቅንብር ባለሙያ መሆኑንም በየሙዚቃወቹ ጣልቃ እያስገባ የሚያቀነባብራቸው ምስሎች ለዚህ ሙያው በቂ ማስረጃ ናቸው።ከንጉስ ኃይለስላሴ የጀኔቫ ንግግር ጅምሮ የታሪካዊ ቦታዎችን፣ የብሄረሰቦች አናኗርና ባህሉን፣ ታሪኩን

ከሙዚቃው ጋር አጣጥሞ አካቶ የሚያቀርባቸው ዝግጅቶች የተዋጣልት ከያኔና የጥበብ ሰው ምደባ ውስጥ አስገብቶታል።

ቴዲ በነዚህ ሥራዎቹ የተነሳ የመናገር ፡የመጻፍ፡የመደራጀት፡ የመሰብሰብ ነጻነት ባልተጠበቀበት ሀገር ገዥዎች ሁሉ ነገር የሚያስበረግጋቸው በመሆኑ እንደሌሎቹ የዲሞክራሲ ተሟጋቾች ሁሉ ቲዎድሮስ ካሳሁንም ከእነርሱ ጥርስ ማምለጥ አልቻለም ፡ ምክንያት የማያጣው የውያኔ አገዛዝ ሰበብ ፈልጎ፡ በተቀነባበረ ሴራ ለእስር ዳረገው። በይስሙላ ፍርድ ቤት ውሳኔ አካላዊ እንቅስቃሴው ተገታ፡አንደበቱ ታሰረ፡ ድምጹ ታፈነ።

ይህ የሕዝብ ድምጽን ማፈን ትልኮው ያደረገው የወያኔ አገዛዝ እርሱን ብቻ ሳይሆን ወደ 30ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን በፖለቲካ እምነታቸው ታስረው፡ በሕገውጥ ማጎሪያ ቤቶች እየማቀቁ ይገኛሉ። የቴዲ ዛሬ መፈታት ለብዙ ኢትዮጵያዊያን አንደ እፎይታ መሆኑ ባይካድም ዛሬ ከተንሹ እስር ወጥቶ ወደ ትልቁ ቢቀላቀልም የተጣለበት ገደብ ግን መልሶ ለማስገባት የተወሰነ ጉዳይ መሆኑን በሚያመለክት መልኩ ነው ተንጠልጥሎ ተፈታ የተባለው። ወያኔ ቴዲን ባመክሮ ሲፈታ ድሮም በውስጠ ወይራ የታሰረበት የሙዚቃ ሥራው መሆኑን በሚያስመሰክርና በሚያረጋግጥ መልኩ ምንም አይነት ጥፋት እንዳይፈጽም ይህን ተላልፎ ቢገኝ ተመልሶ ወደ ማጎሪያ ቤታቸው እንደሚልኩት ኃይለኛ ገደብ አስገብተው ነው ፈታን የሚሉት። የኪነት ሰው የሚሰራቸው ሥራዎች ሁሉ የተለያዩ ትርጉም እየተሰጣቸው በሚስጥር የነጭ ለባሾች በግልጽ የፖሊሶች ወከባና ክትትል ሰለባዎች ናቸው። ታዲያ በሰላማዊ ሂደት እንኳ ለዚህ አይነት አሰራር የተጋለጠ ሙያ በምን ምልኩ ነው ሥራውን በነጻነት ሰርቶ ሁለት አመቱን የሚጨርሰው? እነሱ የማይፈልጉት ነገር ቢያደርግ መልሰው አካላዊ እስራቸውን ለመቀጠል ወስነው ነው አሁን የሚደርስባቸውን የተቃውሞ ግፊት ለማለዘብ የለቀቁት።

ቲወድሮስ አሁንም በሙሉ ኃይሉ የመንቀሳቀስ ነጻነቱን ገድበው ነው ከእስር ፈታንህ ያሉት። ይህ ብቻ አይደለም እስሩን ያለ አመክሮ ቢጨርስ ቀሪው ስምንት ወር ብቻ ነው፡ የተሰጠው ገደብ ግን ሁለት አመት የሚል ነው። ልብ በሉ ከዚህ ላይ ያለውን የሕግ መፋለስ ለሙያተኞች ትቼ እንዲሁ ገለባ ገለባውን ድብቅ ተንኮል እንኳ ብመለከት ቴዲ ገደቡ እስከሚያልቅ የሚደርስበትን የህሊና መሸማቀቅ በሥራው ላይ የሚያመጣውን ጫና አስቡት፡ ቲወድሮስ የተሰማራበት የሙያ አይነት በተንኮል የበሰለው የመለስ ሕሊና የቴዲ ገድብ ሊያልቅ ትንሽ ቀናት ሲቀረው ሰበብ ፈልገው ቢያስገቡት የሚጎዳው ቴዲና ታዳሚዎቹ ናቸው። በመሆኑም በዚህ አመክሮ የተተቀሙት ወያኔዎች እንጂ ቴዲ አይደለም።ስለሆነም ልክ እንደብርቱካን ሚዴቅሳ የምህረት ማንሳት ፖለቲካ ውስጥ ተለጉሞ የተፈታ መሆኑን ልብ ልንል ይገባናል ። ይህ ከሆነ አሁንም ቴዲን ጨምሮ ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱ ትግሉ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ቴዲ ተለጎመ እንጅ አልተፈታም።